# ዓለማየሁ ገብረማርያ ተብየው
# የኢትዮጵያን ሕዝብ ፀረ_ወያኔ አመፅ ለማጨናገፍ
# በማሻጠሩ ቅሌትን በገዛ እጁ ተከናነበ
# ውጉዝ ሆነ

ከአስተዋይ በቀለ

የቅሌትን ቁልፍ በእጁ አጥብቆ የያዘው የኢትዮሚዲያው ዋናው ወደላ ፣አብደላ ቄስ መምሬ ዓለማየሁ ገብረማርያም ተብየው ፣ለተበደለች ኢትዮጵያና ለተጐሳቆለው ሕዝቧ በእውነት የሚያስብ፣ የፖለቲካ ክብርና ጽንዓት ያለው ቅን መንገድ ሳይሆን፤ የባእዳን ተልእኰ እኩይ ተግባር መመላለሻ  ዋና አውራ ጐዳና ሆኖ ይታያል።

በቅርብ ለሚከታተለው ሰው ደግሞ በባእዳን መሰሪ ተንኰልና ተልእኰ እንደ ኢጋሰስ ተጭኖ የሚነዳ ፖይንትማን ይመስላል ።

በሰፌድ ለሚያበጥረው፣ በዓይነ_ልቦና ወንፊት ለሚነፋው፣በእዝነ_ልቦና ወንጠፍት ለሚያጠለውማ ! መላዕክተ_ሊቀ_ባዕዳንነቱ ከባድ ዝናብ እንዳዘለ ጉም ቁልጭ ብሎ ይታይ ይሆናል ።

በኢትዮጵያ አንጻር ግን፣ ለእውነት በመቆም የመሰዋዕትነት ሕይወት ለመምራት የገባው ቃል ኪዳን የለውም። እንደ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ይከዳል ወይም እንደ ዩሐንስ ጨርቁን ጥሎ ይሸሻል እንጂ አንድ ጠብታ ደሙን ለአገራችንና ለሕዝባችን አያፈስም ።

በውል የማታውቁት አገር ወዳዶች ካላችሁ፣ይኸ ሰው በለይኩን ፈቃዱ ሳይሆን፣እንደ ኀብስት ሙክክ ብሎ የበሰለ ክሬዴንሻል ጉድለት ምክንያት ለከት የሌለው፣ የተዝረከረከና ቅኖችን የሚያስት ጹሑፎች ሳያምጥ፣ ሳያላምጥ፣ ሳያመነዥክና ሳያባዝት እስከነ ጥፍ_ጥሬው የሚተፋ የኢትዮሚዲያ መደበኛ ለቅላቂ ነው ። የለቀለቀውን ጹሑፎቹን መከታተልና ማንበብ ማለት ከወፈፍተኛ ጋር መጓዝ ማለት ነው ።

ሲያሰኘው  አል ገብረማርያም ነኝ ይላል። እሱ የራሱ ጉዳይ  ! ነገር ግን የድንቁርናውን የራስ ዘውድ አጥልቆ ካሊፎርንያ እሳተ ገሞራ ላይ ከተዋቀረው ታዛው ሆኖ ከዚህም_ ከዚያም የፖለቲካ ጉዳዮችን ቁንጣ_ቁንጢ ቃላትና ሐረጐችን እየለቃቀመ እንደናስ የሚጮህ፣ ሃሴት የሚያደርግና የሚቀጥፍ ተልእኮው ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ሉዓላዊነት እጅግ ጠንቅ የሆነ አደገኛ መስመር ነው ።

ከአዳዋው የባዕድ ቅጥረኛ ከባንዳው  መለስ ሞት ወዲህ ደግሞ በጣም ተነስቶበታል ። ልበ በሽተኛነቱና አፈ _ሞጥሟጣነቱ ያውዘገዝገዋል።

የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ፣ ሕግና ፖለቲካ ፉት ያልኩ፣ በእውቀትና በምክር የከበርኩ፣ የበጎች ጠባቂ መድኃኔ_ሕዝብ ፣የኢትዮጵያን ልብ የምመዝን ዋናው የፖለቲካ መሐንዲስ እኔ ነኝ እያለ ወደ ሰማይ እንደሚጐን ንስር ክንፍ አውጥቶብናል።

የባእድ ጌቶቹ ወዳጅ ሲዳከም አትርሳው የተባለ ይመስል ምዉታን ቀጠና ገብቶ ላለቀለት ወያኔ_ኢህአዴግ ተቆርቋሪ ምስለኔ ሆኖብናል።

ወያኔ_ኢህአዴግን አገር ለከፈለ፣ ድንበር ላስቆረሰ፣ ሕግ ላፈረሰ፣ ሕዝብ ለበደለ ጽድቅ ይገኛል ሲል፤ ተቃዋሚውን ወገን ደግሞ ያገራችሁንና የሕዝባችሁን ነገር ትታችሁ ማንዴላ እንዳደረገው ይቅር ተባብላችሁ ለብሔራዊ ውይይትና ብሎም ከወያኔ ጋር በሠላም አብሮ ተቻችሎ ለመኖር ቅረቡ በማለት ሕዝባዊ አመፅ አጨናጋፊ ጥሪ አቅርቦ ለማስፈጸም ይሯሯጣል ።

በእርሱ ቤት የማይታወቅበት መስሎት እውነት ተናጋሪ፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ነኝ ይላል። አልገባውም እንጂ እሱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሚታወቀው መጀመሪያ ቅንጅትን በስውር በመስለቡና በማስፈረሱ ቀጥሎም ወተት መግፋት ቅቤ ያወጣል እያለ ከወያኔ_ኢህአዴግ ሥርዓት ጋር ወግኖ ኃይለማሪያም ደሳለኝን እንጀራ አብይ፣ ውሃ አጠጪና ፈገግ በል ባይ መካሪ ፕሮቶኮል በመሆኑና በአገርና በሕዝብ ጉዳዮች ላይ ባሳየው ቅሌትና ባንዳነት ነው ።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጥቃት ያወጀበት ዓለማየሁ ገብረማሪያም ጧ_ፈንዳ ይላል እንጂ ወይም እንደ ፍልፈል እንዲያው በከንቱ በባንዳነት ይታከታል እንጂ፤ ኢትዮጵያ እንደሁ በራሷ ሕዝብ አመጽ፣ በጻድቃንና በነቢያት ልጆችዋ ፀሎት ከባዕዳን ተልእኮ አውድማነት፣ ከወያኔ_ኢህአዴግ ዘረኛ ሥርዓትና ባሕል ሁሉ ሙሉ በሙሉ ነፃ ወጥታ ጥሩ ቀን ታያለች ። ያኔ እርሱንና መሰሎቹን አያድርገኝ ።

ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅዓላማችን
ከወያኔ_ኢህአዴግና ከስውር ባንዳዎች ጋር አይደራደርም !

ብሔራዊ ሉዓላዊነትና የሕዝብ የበላይነት በአመጽ ይረጋገጣል !!

ጠላት ሁሉ ይደመሰሳል!